᎑
# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቀደም፡፡

ቁጥር 29 ቀን 17.11.67


## ዲሞክራሲና የመደራጀቱ ጉዳይ

ዲሞክራሲ ዛሬ የሰፊው ሕዝብ የትግል መፈክር ነው፡፡ አድሃሪ ሃይሎች ተደራጅተው ለዘመናት ሰፊውን ዋትቶአደር ሕዝብ በገዙበት፡ የአመጽ ጫናቸውን በሰፊው በዘረጉበት አገር ውስጥ ዲሞክራሲ ልዩ ትርጉም አለው፡፡ ለሰፊው ጭቁን ሕዝብ ዲሞክራሲ የመደራጃ እርካቡ ነው፤ የኑሮ ዋስትናው ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬ የዲሞክራሲ ጥያቄ ዋና የትግል ጥያቄ ነው፡፡

በአገራችን ታሪክ ውስጥ መቼውንም ቢሆን ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የደረሰበት ጊዜ አልነበረም፡፡ በባሪያ ስልተምርት ላይ የቆመውንና ምናልባትም እንደጥንት ግሪኮች ህብረተሰብ ለ'ጨዋው' መደብ፡ ለባለባሪያው፡ ለ'ዜጋው' ዲሞክራሲን ሳይሰጥ ያልቀረውን የአክሱምን ስልጣኔ፤ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በፊት ላንድ ሁለት አመት ያህል የነበረቸውን የጋዜጣ ነፃነትና እንደገዳ ባሉ ባንዳንድ የቀድሞ ባህላዊ አስተዳደሮች ውስጥ የነበሩትን አንዳንድ ዲሞክራሲያዊ መልክ የነበራቸውን አሰራሮች ወደጐን ብንተው ኢትዮጵያ በፍፁም ዲሞክራሲን አላወቀችም ለማለት እንችላለን፡፡ ያገሪቲዋን አስተዳደግ ታሪክ ስንመለከትም ይህ ሁኔታ ፍፁም አያስደንቀንም፡፡

ምኒልክ የንጉሰነገስቱን መንግስት ከመፍጠራቸው በፊት በአበሻ አገርም ሆነ በሌሎች የአስራዘጠነኛው ክፍለዘመን መንግስታትና ሱልጣናት የነበረው ቢደረጅ ፊውዳላዊ፡ ያለዚያም ከዚያ የሚቀድም ስርአት ነበር፡፡ ዲሞክራሲ ከከበርቴው ስርአት ጋር የሚመጣ ስለሆነ በነዚያ ባለፉት ህብረተሰቦች ውስጥ ሊታይ ይችል ነበር ተብሎ አይገመትም፡፡ የምኒልክም የንጉሱነገስት መንግስት በፊውዳላዊ ስርአት ላይ የቆመ፡ እንዲያውም ይህንን ስርአት ከአበሻው አገር ወደደቡቡ ያዘመተና ያስፋፋ መንግስት ነበር፡፡ የኢምፔሪያሊዝም በዘመኑ መግባት ይህንን የንጉሰነገስቱን መንግስት መሰረታዊ ባህርይ አላለወጠውም፡፡ የሃይለስላሴ ዘመንማ በትክክል 'ፊውደ—ፋሽስት' ተብሎ ተጠርቶአል፡፡ ፊውዳላዊና ፋሽስታዊ ያድሃሪያን የአመጽ አገዛዝ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ መቼውንም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብንም ሆነ አሰራርን ለማግኘት እድል አላጋጠማትም፡፡

ይልቁንስ ኤርትራ ለአስር አመታት ያህል በእንግሊዞች ስር በነበረችበት ጊዜ ዲሞክራሲን በመጠኑም ቢሆን አይታለች፡፡ በነዚያ አስር አመታት ውስጥ በኤርትራ የንግግር፡ የጽሁፍ፡ የመደራጀት ነፃነቶች ነበሩ፡፡ ነፃ ጋዜጦች፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፡ የሙያና ሌሎችም ሕዝባዊ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትያዝ በተወሰነበት ወቅት፡ የራስዋ ህገመንግስት ዲሞክራሲያዊ ከመሆኑ የተነሳ፡ የሃይለስላሴም መንግስት ቢያንስ በወረቀት ዲሞክራሲያዊ ለመምሰል እንዲችል 'የተሻሻለውን' ህገመንግስቱን እንዲያወጣ ተገዶ ነበር፡፡ ይሁንናም፡ እንደሚታወቀው ሁሉ፡ የሃይለስላሴ መንግስት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በመፍቀድ ኢትዮጵያን ወደኤርትራ ደረጃ ከፍ በማድረግ ፈንታ የኤርትራን ነፃ ጋዜጦች፡ የሙያ ድርጅቶችና ፓርቲዎች አንድ ባንድ ደመሰሰ፤ ኤርትራን አቁርቁዞ ወደኢትዮጵያ ደረጃ አወረዳት፡፡ ይህም በኤርትራና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ የተፈፀመ ፋሽስታዊ ወንጀል እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

በመጋቢት 3 ቀን 1967 'ኢትዮጵያ ለዜጎችዋ ሁሉ እኩል ናት' በሚለው መግለጫው ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት በኤርትራ ያን ጊዜ ስለነበረው ዲሞክራሲ በበኩሉ የሚከተለውን ይጽፋል፡—

> '... በዚሁም /ማለት በከፋፍለህ ግዛ —ሰሕዴ/ ተንኮል ምክንያት የቀበሌው ሕዝቦች በሃይማኖት ልዩነት ላይ በተመሰረተ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ቡድን ተከፋፍለው እርስ በርስ ሲታገሉ ኖሩ፡፡ ቅኚ ገዥዎቹ ያንን የርስበርስ ትግልና በዜጎቹ መካከል ያለውን ልዩነት በድርጅት መልክ ቀርጾ ኗሪ የሚያደርገውን መሳ የዲሞክራሲ ስርአት የሚል አወናባጅ ስያሜ ሰጥተውት ነበር፡፡.....'

ከዚያም የመንግስቱ መግለጫ እንዴት ይህ የርስ በርስ ትግል የኤርትራን ሕዝብ እንዳዳከመውና እንዴት የፖለቲካ ቡድኖች በገንዘብ እንደተሸጡ ከተናገረ በሗላ፡—

'...ሆኖም በዚያን ጊዜም ቢሆን የሰፊው ሕዝብ ድጋፍ ከሗላው የነበረና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ስሜቱ በቅኝ ገዥዎች ዱለሳ ያልላሸቀው የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ያንድነት ማህበር የራሱን የፖለቲካ ቡድን የነፃነት ማስገኛ ግንባር አድርጉት ነበር...' ይላል።

በዚያው ባንዱ መግለጫ ውስጥ በሚገኙትና በጥቂት አረፍተነገሮች በሚራራቁት በነዚህ ሁለት ጥቅሶች መካከል ያሉትን አይናውጣ ቅራኔዎች ማንም ባንዴ ሊያያቸው ስለሚችል እዚህ ላይ በዝርዝር እንመለከታቸውም። የቀሩት የዚያን ጊዜ የኤርትራ ፓርቲዎች 'በሃይማኖት ልዩነት ላይ' የተመሰረቱ ሲሆኑ ይህኛው መግለጫው የሚያሞግሰው ፓርቲ ግን 'የነፃነት ማግኛ ግንባር' ነበር! እነዚያኞቹ በገንዘብ በቅኝ ገዥዎች የተገዙ ሲሆኑ ይህኛው ግን ከሃይለስላሴ መንግስት ምንም ጉቦ አልተቀበለም ነበር! ቅኝ ገዥዎች የፈጠሩት 'ዴሞክራሲ' የሚባል መሳ እነዚያኞቹ ሲጠቀሙበት እንደወንጀል፡ እነዚህኞቹ ሲጠቀሙበት ደግሞ እንደተቀደሰ ስርአት ይቆጠራል።

መቼስ ይህ የመንግስቱ መግለጫ የኤርትራን የፖለቲካ ታሪክ ፍፁም አጣምሞ እንዳቀረበ ግልጽ ነው። ባጭሩ ነገሩን ለማቃናት ያህል፡ እንግሊዞች ከኤርትራ ሊወጡ ሶስት—አራት አመት ሲቀራቸው በኤርትራ ቢያንስ ስድስት የታወቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነበሩ። 1ኛ/ የመንግስቱ መግለጫ የጠቀሰው 'ዩኒየኒስት ፓርቲ' የክርስቲያኖች ሆኖ በርግጥም ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድን የሚጠይቅ ነበር። 2ኛ/ የኤርትራ እስላሞች ማህበር —'ኤሪትሪአን ሞዝለም ሊግ'— ቢቻል ወዲያውኑ ለሙሉ ነፃነት፡ ያለዚያም ለአስር አመታት በኢንተርናሽናል ቁጥጥር ስር ለመኖር ይታገል ነበር። 3ኛ/ ሊበራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ የክርስቲያኖች ሆኖ ቀስ በቀስ በተባበሩት መንግስታት ቁጥጥር ስር ነፃነትን እናገኝ ይል ነበር። 4ኛ/ ያዲሲቱ ኤርትራ ቡድን በጣሊያኖች ቁጥጥር ስር ለተወሰነ ጊዜ ቆይተን ነፃነትን እናገኝ ይል ነበር። 5ኛ/ የምጽዋ የእስላሞች ብሄራዊ ቡድን ለሌሎች አስር አመታት በእንግሊዞች ስር ቆይተን ከዚያ በሗላ ነፃ እንውጣ የሚል ነበር። 6ኛ/ ያርበኞች ማህበር የተባለው ድርጅት ደግሞ 'በፖለቲካ ውስጥ ሳይገባ' የአባሎቹን መብት ለመጠበቅ ብቻ የቆመ ነበር። ከነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ ከመጀመሪያው በስተቀር፡ የቀሩት አብዛኞቹ ከሃይለስላሴ ፊውዳሊዊ የንጉስ ነገስት መንግስት ጋር መዋሃድን በጥብቅ ይቃወሙ ነበር።

ለማንኛውም ግን፡ የሃይማኖትን ባንዲራ ቢያውለበልቡም፡ ወይንም ያውለበለቡ ቢመስሉም ሁሉም የቆሙት የመደብ ጥቅምን ለመጠበቅ መሆኑን የፖለቲካ ሳይንስ ሀሁ ያስተምረናል። በማንኛውም ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ከሃይማኖቶች መፈጠር ጀምሮ በሃይማኖቶች መካከል የተደረጉት ጦርነቶች የጥቅም ጦርነቶች ነበሩ። ያውሮፓውያን ክሩሴድስ ሆኑ የእስላም ሃይማኖት ታላላቅ ወረራዎች፡ በኢትዮጵያም ለሶስት መቶ አመታት ያህል፡ ከአስራ ሶስተኛው እስከአስራ ስድስተኛው ክፍለዘመን፡ በአበሻው መንግስትና በምስራቅ የሱልጧናት መንግስታት መካከል ተደጋግመው የተደረጉት ጦርነቶች ሃይማኖትን የመስለፊያ ባንዲራ አደረጉት እንጂ ዋናው ምክንያታቸው የጥቅም፡ የኢኮኖሚ በላይነት ፍላጎት ነበር። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትም የኤርትራ የቀድሞ የፖለቲካ ማህበራት እንደዚሁ የመደብን ጥቅም ለመጠበቅ የቆሙ ነበሩ።

ይህ ሆኖ ሳለ ከላይ የጠቀስነው የወታደራዊው መንግስት መግለጫ የሚያሳየው አንድ ዋና ነገር ቢኖር የደርጉ 'ብሄረኛነት' —'የኢትዮጵያ አንድነት ፍፁምነት'— እስከምን ድረስ አይኑን አሳውሮት የዴሞክራሲን ትርጉምና ጥቅም እንዳያይ እንዳደረገው ነው።

ወደዋናው አርእስታችን እንመለስና እንግዲህ ኢትዮጵያ መቼውንም ቢሆን ዴሞክራሲን ከስራ ላይ ለማዋል እድል እንዳላገኘች አሁንም እናስታውስ። የየካቲት እንቅስቃሴ እንደፈነዳ ግን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የዴሞክራሲ ፕሪንሲፕል ታይቶ ነበር። የአከሊሉ መንግስት እንደወደቀ መላው ያገሪቱ ሕዝብ፡ መላው የነቃው የህብረተሰባችን ክፍል፡ ወዛደሩ፡ ንኡስከበርቴው፡ ገበሬውና በጠቅላላው ሰፊው ሕዝብ የዴሞክራሲን ጥያቄ አጣዳፊ ቢሆነ መንገዱ፣ አቅርቦ ነበር። ለጥቂት ጊዜና በመጠኑም ቢሆን ዴሞክራሲን በቀጥታ በስራ ላይ ማዋል ተጀምሮ ነበር። የዛሬን አያድርገውና የካቲት 19 ቀን 1966 ሁለተኛው ክፍለጦር አስመራን ይዞ ለንጉሡ ካቀረባቸው 23 ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ

የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ነበር:: የዛሬን አያድርገውና: የካቲት 21 ቀን 1966 አራተኛው ክፍለጦር በአዲስ አበባ ላይ ባሰራጨው የ11 ነጥቦች በራሪ ወረቀት በመጀመሪያ ደረጃ የጠየቀው የንግግርን: የጽሁፍን: የመሰብሰብን ወዘተ. ዲሞክራሲያዊ መብቶች ነበር:: ባለፈው አመት በመጋቢት ወር በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ለጥቂት ሳምንታት ሰፍኖ ነበር:: ያኔ ብቅ ያለቸው የዲሞክራሲ ጭላንጭል እየመነመነች: እየተዳከመች ሄዳ መስከረም 2 ቀን 1967 ላይ ተነጥራሹ ድርግም አለች:: ያ ሁሉ የየካቲት ተስፋ እንዲያ ሲቀጭ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሃይለስላሴን የመሰለ ፋሺስታዊ ፈላጭ ቆራጭ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጫንቃ ሲወርድ፣ ሰፊው ሕዝብ ከዋይታውና ከፈንጠዚያው የትኛውን መምረጥ እንደሚገባው ማወቅ ተስኖት ነበር:: እንደሚታወሰውም ይህ የተቃራኒ ድርጊቶች ባንድ ላይ መምጣት በተራማጁ የህብረተሰባችን ክፍሎችም ውስጥ ታላቅ ውዥንብርን ፈጥሮ ነበር::

ፊውዳሊዝም የጨለማ ስርአት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ስርአት ውስጥ ሰፊው ሕዝብ በምንም አይነት ስለራሱ የወደፊት እድል አንዲት ቃል እንኳን እንዳይተነፍስ፣ ስለትምህርቱም ሆነ ስለባህሉ: ስለአስተዳደሩ: ስለኢኮኖሚው: ስለፖለቲካው: ባጭሩ ስለማንኛውም የህብረተሰብ ጥያቄ አሳብ እንዳይሰጥና ከላይ የተወሰነው ብቻ በግድ: በፋሺስታዊ አመጽ እንዲፈፀምበት ተደርጐ ኖሮአል::

እንደዚህ አይነቱ ፀረዲሞክራሲያዊ ስርአት በሰፈነበት አገር: ሕዝቡ አሳቡን የሚያገኘው ከአፍ ወደጆሮ በሚተላለፈው: አስር ጊዜ ተለዋውጦና ተጣምሞ በሚቀርበው የመንደር ወሬ ነው:: የሃይለስላሴ መንግስት እራሱ የመንደርን ወሬ መልቀምንና እራሱም ፈጥሮ ማሰራጨትን እንዳገዛዝ ዘዴ ሲጠቀምበት እንደነበር ይታወሳል:: የጊዜው ወታደራዊ መንግስትም የመንግስትን ስልጣን በተግባር ከጨበጠበት ከሰኔ 26 ቀን 1966 ጀምሮ እስከዛሬ 'የሃሰት ወሬ' የሚያሰራጩትን ለመቋቋም ብዙ ወትውቶአል:: ታዲያ እራሱስ በየጊዜው አውቆ ያሰራጫቸው የመንደር ወሬዎች የሉም ወይ? ራሱስ ልክ እንደ ሃይለስላሴ መንግስት የሃሰት ወሬ ከማሰራጨት መቼ ነፃ ሆኖ ያውቃል? ከዚህም የባሰ ግን: ዲሞ''ራሲ ባገሪቱ ስለሌለ: ፊውዳላዊ በሆኑት የርስበርስ ትውውቅ: የወዳጅነት: የምልጃ: የመንደር ወሬ ዘዴዎች በመጠቀም ስንቶን አድሃሪ በየስልጣን በታው ሹሟል::

በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኑሮና አሰራር ስለማይታወቅ ሌላው ቀርቶ ይህ የምንሰራበት ያማርኛ ቋንቋ እንኳን ፊውዳላዊ ዘዴዎችን እንዳዘለ እንዲቀይ ሆኖአል:: የአበሻው ፊውዳላዊ ስርአት የፈጠረው ባህል በቀጥታና በማያወላውል ቋንቋ ለማለት የሚፈልጉትን ነገር መናገርን አይፈቅድም:: እንዲያውም ተቃውሞም ሆነ ሂስ በተቻለ መጠን በተሸፋፈነ ቋንቋ: በእንቆቅልሽ ቋንቋ እንዲቀርብ ይገደድ ነበር:: ነፃ ውይይትና ክርክር መቼውንም ቢሆን አልነበረም:: አሁንም አሳቡን ያለአንዳች ተጽእኖ ባደባባይ ለማቅረብ የሚችለው ወታደራዊው መንግስት ብቻ በሆነበት ሰአት ሰፊው አምራች ሕዝብ ተለጉሞ ከመያዙ የተነሳ ኑሮውን ለማሻሻልም ሆነ አዳዲስ ትምህርቶችን ለመቅሰም ብዙ ችግር አለበት:: የሚገርመው ግን: ይህ በነፃ ለመናገር እርሱ ብቻ መብት ያለው መንግስትም ቢሆን ባንዳንድ አቢይ ያገር ጉዳዮች ላይ ግልጽና የማያወላውል አቋም አላሳየም:: ለዚህ ግን ምክንያቱ የፊውዳላዊው ስርአት ያነጋገር ወግ ተጽእኖ ብቻ አይደለም፤ ያስተሳሰብ ውዥንብርም ነው::

<u>የፖለቲካ ፓርቲው ጉዳይ</u>:-

ያስተሳሰብ ውዥንብርን ቁልጭ አድርገው ከሚያሳዩት ያገር ጉዳዮች አንዱ የመንግስቱ የፖለቲካ ፓርቲ ጉዳይ ነው:: የፖለቲካ ፓርቲ ወይንም ፓርቲዎች ጉዳይ በነዚያ በጥቂቶች የዲሞክራሲ ሳምንታት በመንግሥቱ ጋዜጦች በነፃ የተተቸበት ቢሆንም በመንግስት ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳው በታህሳስ 11 ቀን በወጣው 'የህብረተሰባዊነት መመሪያ' ነበር:: በዚህ 'መመሪያው' ውስጥ ጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት አንድ 'በህብረተሰባዊነት ፍልስፍና የሚመራ መደበኛ የሆነ መላውን ሕዝብ የሚስብና የሚያስተባብር ብሄራዊ የተራማጆች የፖለቲካ ህብረት መኖር አለበት' አለ:: 'መደበኛ' የሚለው ቃል ውዥንብርን ማስከተሉ አልቀረም:: መደበኛ ከተባለ: ከፈለጉ ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ ማለት ይሆን የሚል ጥያቄ አስነስቶአል:: 'የተራማጆች የፖለቲካ ህብረት' የተባለውስ ምን ይሆን? 'መመሪያው' እራሱ ከፍ ብሎ 'የፖለቲካ ማህበር' ያለው ነው? ታዲያ እርሱ ልዩ ልዩ አስተሳሰብ ያላቸውን

ተራማጅ ግለሰቦች የሚያስተባብር 'የግለሰቦች ግንባር' ማለት ነው? ወይንም ደግሞ 'ማህበር' ማለት እዚህ ላይ ፓርቲ ማለት ከሆነ፣ በፍጥረቱ ያንድን መደብ ጥቅም ብቻ ለመጠበቅ* በግለሰቦች ፈቃደኛነት ብቻ በነፃ የሚቋቋሙ የፖለቲካ ፓርቲ እንዴት በአዋጅ ይፈጠራል? መመሪያው አዋጅ ከሆነ ማለት ነው::'መላውን ሕዝብ የሚሰብና የሚያስተባብር' ከተባለ ምናልባት ልዩ ልዩ ፓርቲያቸንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን —ማስ ኦርጋናይዘሽንስ— የሚያቀፍ ግንባር ማለት ይሆን?

እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች እስከዛሬ ሳይብራሩ ቀርተዋል::እንዲያውም ወታደራዊው መንግስት ወይንም አንዳንድ የደርግ አባሎች በየጊዜው ባደረጓቸው ንግግሮችና ባወጡአቸው መግለጫዎች ነገሩን ከባሰ ውዥንብር ውስጥ ከትተውታል::

ይህንን ሁኔታ ለማሳየት በአንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌ እንጀምር:—

የደርጉ ዋና ሊቀመንበር ባለፈው ሰሞን በሃረርጌ ክፍለአገር ለወታደሮች ባደረጉት ገለፃ ውስጥ ስለአብዮቱ መጨረሻ ግብ ሲገልጡ 'በዚህ እርምጃ /ማለትም አድሃሪዎችን በየቦታው በመያዝ—ስሕድ/ ጭቁኑ ሕዝብ ነፃነቱንና እኩልነቱን እንዲጨብጥ ከአደረግንና መብቱ ከተረጋገጠለት በሗላ የሚጠብቀን ታላቅ አላፊነት አንድ ራሱን የቻለ ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅት/ፓርቲ/ ማቋቋም ነው' ብለዋል::ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ መሰረታውያን መብቶችን የሚያቀፍ አዋጅ በመዘጋጀት ላይ መሆኑንና ይህም አዋጅ ተዘጋጅቶ ሲወጣ አፈር ገፊውን ገበሬ:ወዝአደሩን:ምሁራንና ተማሪዎችን የሚወክሉ: 'በህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ መመሪያዎች መሰረት የተደራጁ ማህበራት በዚህ በተባለው አንድ ብሄራዊ ፓርቲ ተጠቃለው አገር የማስተዳደርን ስልጣን ከመለዩ ለባሹ ሰራዊት እንዲረከቡ ይደረጋል...' ብለዋል::

በመሰረቱ:ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲፈጠርና የፈለገ ሁሉ:የቻለ ሁሉ እንደየመደብ ጥቅሙና ርእዩተአለሙ:በፓርቲያቸም ሆነ በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ እንዲሰበሰብ የሚደረገው፣ ሰፊው ሕዝብ ታግሎ ጠላቶቹን —ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን— በአብዮታዊ ሃይል ከደመሰሰ በሗላ 'ነፃነቱንና እኩልነቱን' ለመጨበጥና 'መብቱን' ለማረጋገጥ እንዲችል ነው::ሰፊው ሕዝብ የራሱን ነፃ ድርጅቶች ሳያቋቁም:አቋቁሞም ሳይታገል በምንም አይነት ተአምር ነፃነቱንና እኩልነቱን ሊያገኝ አይችልም:: ነፃነቱንና እኩልነቱን የሚያስጨብጠውና መብቱን የሚያረጋግጥለት የገዛ ሃይሉ እንጂ ወታደራዊው መንግስት አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም::የራሱ ነፃ ድርጅቶች ከሌሉት ሰፊው ሕዝብ ምንም አያገኝም፣ ያለተጋድሎ ከላይ የሚሰጠው አንድም ነገር የለም::በሊቀመንበሩ አባባል ማሰረቻ. ግን ነፃነትንና እኩልነትን ሰጭው ወታደራዊው መንግስት ሲሆን 'ብሄራዊው የፖለቲካ ድርጅት' የሚቋቋመው ግን ለንኡስ ከበርቴው ወታደራዊ መንግስት 'ተቀባይነት ያለው' ሽፋን ለመስጠትና ትግሉን ለመግራት ያህል እንጂ ለአብዮቱ መግፊያ አይደለም::

'ነፃነት:እኩልነትና መብት' የመራራ ትግል ውጤቶች እንጂ በቀዳሚያ ከመንግስት የሚሰጡ ነገሮች አይደሉም::ደግሞም በኢትዮጵያ እነዚህ ቃላት ሙሉ ትርጉማቸውን የሚያገኙት ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም:ከላይ እንዳልነው ሁሉ:በአብዮታዊ ሃይል ከተደመሰሱ በሗላና ሕዝባዊ ስርአት ሲቋቋም ብቻ ነው::ለዚህም የመጨረሻውን ድል በር የሚከፍተው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዋና ጥያቄ የሆነው <u>የዴሞክራሲ ጥያቄ</u> ነው::ቀደም ተከተሉ እንግዲህ መጀመሪያ ዴሞክራሲያዊ መብቶች:ከዚያም ካሁኑ ይበልጥ የጋለና የተደራጀ ሕዝባዊ ትግል:ከዚያም 'ነፃነት:እኩልነትና መብት' ነው::

በጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት አስተሳሰብ ውስጥ ያለውን የቀደም—ተከተል መናጋት አልፈነው ዋናው ሊቀመንበር ቀጥለው የሚያቀርቡትን አሳብ ብንመለከት አሁንም ውዥንብር እንዳለ እንረዳለን::ሊቀመንበሩ 'መሰረታውያን መብቶችን የሚያቀፍ አዋጅ በመዘጋጀት ላይ ነው' ብለዋል::ማንም እንደሚያውቀው 'መሰረታውያን መብቶች' የሚባሉት የንግግር: የጽሁፍ: የመሰብሰብ: የመደራጀት ወዘተ. ዴሞክራሲያዊ መብቶች ናቸው::እንግዲህ . . የተባለው አዋጅ እነዚህን መብቶች የሚያቀፍ ከሆነ

---

* ባንዳንድ የከበርቴ ስርአቶች:ሰፊውን ሕዝብ ለማወናበድ ይመች ዘንድ አንዱ መደብ ሁለት—ሶስት ፓርቲያችን ይፈጥራል::በመሰረቱ ግን ፓርቲ ያንድ መደብ የጥቅም መጠበቂያ መሳሪያ ነው::

"አንድ ፓርቲ" ከሚለው የመንግስቱ ምኞት ጋር እንዴት ሊታረቅ እንደሚችል ፈጽሞ አይታየንም:: የተባሉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከላሹና እንደ ሃይለስላሴ መንግስት ህገመንግስት ለይስሙላ የሚታወቁ የበጣሽ ወረቀት ጉዳይ ካልሆኑ በስተቀር ማለት ነው::እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና አንድ ለብቻው የሆነውን የመንግስት ፓርቲ በዚያው ባንዱ አዋዱ ለመመስረት አይቻልም::

በተረፈም እንደሊቀመንበሩ አነጋገር ይህ ፓርቲ የወዝአደሩን: የአፈር ገፊውን ገበሬ: የምሁራንና ተማሪዎችን "በህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ መመሪያዎች መሰረት <u>የተደራጁ ማህበራትን</u>" /ሰርዝ -ሰሕዱ/ ያጠቃልላል ሲባል ሻለቃ መንግስቱ ግንቦት ፫ ቀን "ለአፋር ሕዝብ ተወካዮች" ካደረገው ንግግር ጋር የሚሄድ አይደለም::በዚያ ንግግር ውስጥ ሻለቃው:-

"በፖለቲካ ረገድ የሆነ እንደሆነ በፍልስፍናችን መሰረት ወደፊት የሚቋቋመው የሕዝብ መንግስት በአንድ ተራማጅ የፖለቲካ ማህበር የሚመራ ነው::<u>ይኸም ተራማጅ የፖለቲካ ማህበር በአፈር ገፊው ገበሬና በወዝአደሮች ብቻ የተገነባ ይሆናል</u>::የመንግስት ባለስልጣን የሚሆኑትም በዚሁ የፖለቲካ ማህበር ክልል ውስጥ ያሉት የወዝአደሩና የገበሬዎች ማህበር አባሎች ይሆናሉ.." ይላል::/ሰርዝ -ሰሕዱ/

እዚህም ላይ ውዥንብር ተፈጥሮአል ማለት ነው::በታህሳስ አስራአንዱ የህብረተሰባዊነት መመሪያና ሻለቃ መንግስቱም:ሌሎችም የደርግ አባሎች አልፎ አልፎ በሰነዘሩአቸው አንዳንድ አባቦች የሄዱን እንደሆነ የመንግስቱ ፓርቲ "የተራማጆች ህብረት":"የተራማጆች የፖለቲካ ማህበር":ማለትም የተመረጡ ሰዎች የሚያቋቁሙት "የግለሰቦች ግንባር" ሆኖ እናገኘዋለን::ባሁኑ የሊቀመንበሩ አባባል የሆነ እንደሆነ ደግሞ ነገሩ ከቀላ ጉደል ሕዝባዊ ድርጅቶችን:የሙያ ድርጅቶችን ሁሉ የሚያያዝ "ግንባር" ይመስላል::እንደዚያም ሆኖ እንኳን ይህኛው ግንባር አውቆም ሆነ ባለማወቅ ወደጐን የሚተዋቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች -ለምሳሌ የሃይማኖቶች ተከታዮች ድርጅቶች:የብሄሪሰቦች:የመረዳጃ:የእድር ድርጅቶች- አሉ::

ይሁንናም:የታሰበው እንግዲህ ልዩ ልዩ ማህበራትን የሚያቅፍ ድርጅት ከሆነ የዚህ አይነቱ ድርጅት የመንግስት መስሪያ ቤት እንጂ በምን ተአምር "አንድ ብሄራዊ ፓርቲ" ይሆናል? ልጁን በስሙ በመጥራት ፈንታ:በመንግስቱ ቋንቋ "አወናባጅ ስያሜ" ለመስጠት ካልተፈለገ በስተቀር::ይህም መንግስቱ ሊከተለው የሚፈልገውን የነታንዛኒያን አይነት "ፓርቲያች" ያስታውሰናል::

እነዚህ "ፓርቲያች" በቢሮ ከበርቴውና በንኡስ ከበርቴው መደቦች አባሎች የተሞሉ ቢሮክራሲያዊ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እንጂ የወዝአደሩና የቀረትም ጭቁን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች "ፓርቲ" አይደሉም::በተረፈም:ኢትዮጵያ ታንዛኒያ አይደለችም::በህብረተሰባችን ውስጥ ያሉት የመደብ ትግሎች:ካገሪቱዋ ታሪክ የተነሳ:ሃይለኛና የለየላቸው ናቸው::ስለዚህም የራሳቸውን ጉዳና ይጠይቃሉ::

በሌላ በኩል ግን:የታሰበው ከተባሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች ግለሰቦችን አስመርጦ እነዚህን "የፓርቲው አባላት ናችሁ" ለማለት ከሆነ አሁንም በፍፁም የማያዋጣ መንገድ -የውዥንብር ጉዳና- ተይዞአል ማለት ነው::

1ኛ/ ወደ"ግለሰቦች ግንባር":ወደጥቂት ሰዎች ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ:ወደቢሮ ከበርቴውና ንኡስ ከበርቴው መደቦች ዲክቴተርሺን ሄዱን ማለት ነው::

2ኛ/ የፓርቲ አባልነት እንደሹመት የሚሰጥና የሚገፈፍ ማእረግ ሆነ ማለት ነው::አንድ ግለሰብ ባንዱ ሕዝባዊ ድርጅት በሙያው በተመረጠ ቁጥር የተባለው ፓርቲ አባል ይሆናል፤ በመረጠው ድርጅት በተሻረ ቁጥር ደግሞ አባልነቱ ይቀራል::በሌሎች አገሮች ታሪክ -ሕዝባዊ አብዮቶች ያደረጉትንም አንዳንድ አገሮች ጨምሮ- የዚህ አይነቱ የፓርቲ አባልነት ለጉቦ:ለግል ጥቅም መጠበቂያ:አባልነትን እንደፊውዳላዊ የማእረግ ስም ከአባት ወደልጅ ለማውረሻ መሳሪያ ሆኖአል::ሰፊው ሕዝብ ከንደዚህ አይነት "ፓርቲያች" ምንም ያገኘው ጥቅም የለም::

3ኛ/ ከዚሁ ጋር አያይዞ ማንም ሊገምተው እንደሚችልና በማንኛውም አገር ታሪክ ታይቶ እንደማይታወቅ ሁሉ:የተለያዩ ጥቅሞችን ለማስከበር የሚቋቋሙ የሙያና ሌሎችም ሕዝባዊ ድርጅቶች "በአንድ ፓርቲ":ለአንድ መደብ ጥቅምና ርእዮተአለም መጠበቂያና ማስፋፊያ በሆነ እውነተኛ ፓርቲ

ውስጥ 'ሊጠቃለሉ' አይችሉም፡፡እነዚህ ድርጅቶችና ሌሎችም ፓርቲያቸ በአንድ ፓርቲ ሊመሩ ይችላሉ፡፡ ይህንን ከዚህ በታች እንመለስበታለን፡፡ግን፡'አንድ ፓርቲ' ይፈጥራሉ ማለት ፍፁም ትርጉም የለውም፡፡ ወዝአደር፡ገበሬ፡ምሁርና ተማሪ፡የሃይማኖት መሪ፡ሸማኔና ሸክላ ሰሪ፡የባንክ ሰራተኛና ኩሊ ሁሉም በአንድ የመደብ ጥቅምና በአንድ ርእዮተአለም ላይ ተመስርተው 'ፓርቲ' የፈጠረበት ሁኔታ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፤ ወደፊትም የሚሆን ነገር አይደለም፡፡

ሊቀመንበሩ እንግዲህ የዚህ አይነቱ ባህርዩ በደንብ ያልታወቀ ድርጅት በአዋጅ ተቋቁሞ 'የማስተዳደርን ስልጣን ከመለዮ ለባሹ ሰራዊት እንዲረከብ ይደረጋል' ይላሉ፡፡ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ስለመንግስት ስልጣንና ስለአረካከቡ ያለው አስተሳሰብ፡በየመግለጫውና በየንግግሩ ባደባባይ የወጣው ሁሉ፡አንድ ራሱን የቻለ ያስተሳሰብ ውዥንብር ታሪክ ስለሆነ እዚህ ላይ አንተቸበትም፡፡ ይልቁንስ የኢትዮጵያ አብዮት የግድ መከተል የሚኖርበትን ጉዳና በመጠቆም ጽሁፋችንን እንደምድም፡፡

**አብዮቱ የሚከተለው ጉዳና፡—**

ህብረተሰባዊነት መታወጁ፡ወይንም የመንግስት 'መመሪያ' ሆኖ መውጣቱ ምንም ያህል ሊለውጠው የማይችል ኢትዮጵያ የደረሰችበትና ያለችበት የታሪክ ደረጃ አለ፡፡ይኸውም የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የታሪክ ደረጃ ነው፡፡/በነገራችን ላይ፡'የታሪክ ደረጃ'ሲባል ምን ማለት እንደሆነ እዚህ ላይ ማመልከቱ ይጠቅማል፡፡ሰዎች ፈለጉም አልፈለጉ፡ከልባቸው ምኞት ፍፁም ነፃ በሆነ መንገድ፡ ህብረተሰቦች የግድ የሚራመዱባቸው የታሪክ ደረጃዎች አሉ፡፡በባሪያ ስልተምርት ላይ በተመሰረተ ህብረተሰብ ሶሻሊስት፡ወይንም የከበርቴ/ቡርዧ/ አብዮት ሊደረግ አይችልም ነበር፤ ፊውዳላዊ አብዮት መደረግ ነበረበት፡፡ፍፁም ፊውዳላዊ በሆነ ህብረተሰብም እንደዚሁ ሶሻሊስት አብዮት ሊደረግ ወይንም ወደሃላ ተቀልብሶ ወደባሪያ ህብረተሰብ መምጣት አይቻልም ነበር፡፡ የከበርቴ አብዮት የግድ መከተል ነበረበት፡፡በዛሬይቱ አለምም ግማሽ—ፊውዳልና ግማሽ—የጁ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስርአት በነገሰባቸው እንደኢትዮጵያ ባሉት አገሮች ሶሻሊስት አብዮት ለማድረግ አይቻልም፡፡ የዚህ አይነቱ ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ፡ፖለቲካዊና ማህበራዊ አቋም ሁሉ ይህንን አይፈቅድም፡፡እዚህ በመጀመሪያ ደረጃ ሊከናወን የሚችለው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነው፡፡'የታሪክ ደረጃ' ሲባል እንግዲህ ይህ ነው፡፡/ ይህንን የታሪክ ደረጃ ካልተረዳነውና በምኞት ወይም ባቦሰጡኝ ብቻ ከተራመድን ለህብረተሰባዊነት በር ከፋች እርምጃዎችን በመውሰድ ፈንታ እንዲያውም ለጠቅላላው አብዮት መሰናከል እንሆናለን፡፡

ይሁንናም፡ይህ አብዮት ለምን 'ብሄራዊና ዲሞክራሲያዊ' ተባለ?

አብዮቱ ብሄራዊ የተባለበት ምክንያት ኢምፔሪያሊዝምን ስለሚቃወም ነው፡፡ኢምፔሪያሊዝምን መቃወም ማለትም የባእድ ከበርቴዎችን ኢኮኖሚያዊ፡ፖለቲካዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች ማጥፋት ብቻ ሳይሆን ከነርሱ ጋር የተያያዘውን ያቀባባይ ከበርቴውንና የቢሮ ከበርቴውን መደብም መደምሰስ ማለት ነው፡፡እነዚህ ካልተደመሰሱ ነፃ ኢኮኖሚያዊ ስርአት፡ ነፃ ህብረተሰብ፡ የራሱን እድል በገዛ እጁ ያስገባ ሕዝባዊ ስርአት ለመገንባት ፈጽሞ አይቻልም፡፡ይህ አብዮት በዚህ 'ብሄራዊነቱ'፡ፀረኢምፔሪያሊስት በመሆኑ፡ የአለም ወዝአደሮች ትግል፡ የአለም ሶሻሊስት እንቅስቃሴ አንዱ አካል ነው፡፡

አብዮቱ ዲሞክራሲያዊ የተባለበት ምክንያት ፊውዳሊዝምን ስለሚቃወምና ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚቃወሙትን የህብረተሰብ መደቦችና ሃይሎች ሁሉ አስተባብሮ በአንድ ግንባር ስር ስለሚያሰልፍ ነው፡፡እነዚህ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሁለቱን ጠላቶች ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል የሚተባበሩ ከመሆናቸውም በላይ ሕዝባዊ ስርአት ሲቋቋም በወዝአደሩ መሪነት ስር በመንግስት ስልጣን ይሳተፋሉ፡፡ማለትም፤ ይህ ስልጣን የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲ ያረጋግጣል፡፡

አገራችንን በሚመለከተው በኩል ዋናው የጊዜው ጥያቄ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ነው፡፡ ይህንን ደግመን ደጋግመን ማስታወስ አለብን፡፡እነዚህ መብቶች ከተገኙ ሰፊው ሕዝብ በነፃ ይደራጃል፤ ወዝአደሩ የራሱን መደብ ፓርቲ ያገኛል፤ ሌሎችም ጭቁን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች እንደየሁኔታቸው ይደራጃሉ፡፡ የወዝአደሩ መደብ በፓርቲው አማካይነት ታግሎ የጠቅላላውን ትግል መሪነት ቦታ በመያዝ የጭቁን መደቦችንና የህብረተሰብ ክፍሎችን ሁሉ ግንባር ይፈጥራል፡፡ይህ ግንባር ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በሬቮሉሽናዊ ሃይል ደምስሶ ሕዝባዊ ስርአትን —የአዲሱን ዲሞክራሲ ስርአት—

ያቋቁማል፤ ሶሻሊዝምን ለመገንባት ጽኑ መሰረት ይጥላል። ወደድንም ጠላንም፤ ብዙ መሰናክሎችና ጥምዝምዝ መንገዶች፡አደናጋሪና ለጊዜው መውጫቸው የማይታዩ መጠምዘዣዎች ቢኖሩትም የኢትዮጵያ አብዮት ጉዳና ይኸው ነው፤ ከዚህ ሌላ የለም።

ይህ ከሆነ እንግዲህ፡ወታደራዊው መንግስት በርግጥ ለሰፊው ሕዝብ "እኩልነት፡ ነፃነትና መብት" የቆመ ከሆነ፤ በሃቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማገልገል እንጂ የሕዝቡ አብዮት እንቅፋት ከመሆን ለመቆጠብ ከፈለገ፤ ባሁኑ ሰአት ላገሪቱ ሊያበረክት የሚችለው ታሪካዊ አስተዋጽኦ እንደሚከተለው ይሆናል፡—

1ኛ/ የዚህን አብዮት እውነተኛ ወዳጆችና ጠላቶች በትክክል በመለየት፤ ሰፊው ሕዝብ በተለይም በገጠር የጀመረውን የአድሃሪ መደቦችን ደምሰሳ መደገፍ እንጂ የማይታረቁ ተፃራሪ መደቦችን ለማስታረቅ ከንቱ ሙከራ በማድረግ መሰናከል መሆኑን አሁኑኑ ማቆም አለበት። <u>ገበሬውን በማህበሮቹ አማካይነት በደንብ ማስታጠቅ ያስፈልጋል</u>። በዘማቾች፡በተራማጅ ያገር አስተዳደርና የመሬት ይዞታ ሰራተኞች፡በተራማጅ አዝማቾችና በገበሬ ማህበራት በየገጠሩ መሳሪያዎቻቸውን የሚቀሙትንና ተይዘው የሚታሰሩትን አድሃሪዎች መልሶ መፍታትና ማስታጠቅ መቆም አለበት። በቅርቡ በወሎ አውራጃ እንደተደረገው ሁሉ አንዳንድ አድሃሪ የደርግ አባላት በሃሳብ ከሚስማሟቸው ያስተዳደር ሰዎች ጋር እየሆኑ ፀረሕዝብ የመሬት ከበርቴዎችንና በዝባዦችን በመደገፍ፡ተራማጅ አስተዳዳሪዎችን በማሰር፡የገበሬ ማህበራትንና የፍርድ ሸንጎዎችን በመበተንና የሰላማዊ ገበሬዎችን ቤት እየፈተሹ የመሳሪያ ዘረፋ በማድረግ የሚፈጽሙትን ፋሽስታዊ አመጽ ማውገዝ አለበት፤ ማቆም አለበት፤ የታሰሩትን አውራጃ አስተዳዳሪና የመሬት ይዞታ ሰራተኛ መፍታት አለበት። በልዩ ልዩ ስፍራዎች እንዳደረገውና እንደሚያደርገው ተራማጆችንና፡አድሃሪዎችን ባንድ ቁና በመስፈር፤ የፊተኞችን መጨቆኑን፡ማጉሳቆልና ማሰሩን ማቆም አለበት። እነዚህን የሕዝብ ወገኖች በማንኛውም ቦታና ጊዜ መደገፍ ያስፈልገዋል። በርግጥ አንዳንድ ስህተቶች ከተደረጉ የተሳሳቱት ተራማጆች በምክርና በሂስ እንዲታረሙ ይደረጋል እንጂ የጭቆና እርምጃ ሊወሰድባቸው ፈጽሞ አይገባም። በዚሁም አኳያ በየከተማው በየጊዜው በግፍ ተይዘው የታሰሩት ተራማጆች መፈታት አለባቸው። ለወደፊትም በሆነ ባልሆነው ምክንያት ተራማጅ ግለሰቦችን ይዞ ማሰር መቆም አለበት።

2ኛ/ ባኢምፔሪያሊዝም ላይ አሁኑኑ እርምጃ መውሰድ አለበት። ካሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ጨቋኙ የሃይለስላሴ መንግስት የተፈራረማቸው ፀረአብዮታዊ ውሎች መሰረዝ አለባቸው። በየመስሪያ ቤቱና በየወታደሩ ሰፈርም ውስጥ በ"አማካሪነት"፡በ"አሰልጣኝነት" የተሰማሩት ሰላዮች አሁኑኑ ካገር እንዲባረሩ ማድረግ ያስፈልጋል። የኢምፔሪያሊስቶች ኤምባሲዎች በኤምባሲ ሰራተኛ ስም ወደኢትዮጵያ ያስገቧቸውን ሰላዮችና ሳቦተሮች ማስወጣት ያስፈልጋል። ወታደራዊው መንግስት ለ"እርዳታ"ና ለመሳሪያ ሲል ካሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ለመቆራረጥ እንደማይፈልግ ግልጽ ነው። ነገር ግን ምርጫው ከሁለት አንዱ ነው። ካሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለውን ሽርክና ከቀጠለ ውሎ አድሮ <u>የሕዝብ ጠላት</u> ይሆናል። ካሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ከተቃቃረ ሰፊው ሕዝብ በሚገባ ባልተደራጀበትና ባልታጠቀበት ባሁኑ ሁኔታ ደርጉን ወይንም የደርጉን ተራማጅ ክንፍ ደምስሶ አለም ያለ ፋሽስታዊ አገዛዝን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ይጭናል። ስለዚህ ወታደራዊው መንግስት የኢምፔሪያሊዝምን እግር እየላሰ መኖር ካልፈለገ፤ በርግጥ የሕዝቡን ወገን ከመረጠ በኢምፔሪያሊዝም ላይ ቁርጥ ያለ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፤ ሳይቀደም መቅደም ያስፈልጋል። ይህንንም ማድረግ የሚችለው ሰፊው ሕዝብ በቶሎ የራሱን የትግል ድርጅቶች እንዲያቋቁም በማድረግ ብቻ ነው።

3ኛ/ ወታደራዊው መንግስት የራሱን የመንግስት ቢሮክራሲያዊ ፓርቲ ጉዳይ ወደጎን ትቶ ሙሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማወጅ አለበት። በነገራችን ላይ፤ አሁን ሰሞኑን ሊቀመንበሩ ያደረጉትና ከላይ የተተነተነውን ያንዱ ፓርቲ ጉዳይ ንግግር ኢምፔሪያሊስት አለም ማበረታቻ ባለው ድምጽ በማስተጋባት ላይ ነው። የዚህ አይነቱ ቢሮክራሲያዊ የመንግስት ፓርቲ ለዱአዙር ቀኝ አገዛዝ መሳሪያነት በቀላሉ ለማገልገል እንደሚችል ስለሚያውቁት በርሱም ላይ ቢሆን ተስፋቸውን መጣል ይዘዋል ማለት ነው። ይህ የኢምፔሪያሊስቶች የድጋፍ ድምጽ ብቻ የአቋሙን አድሃሪነት ሊያረጋግጥ ይችላል።

የንግግር፡ የጽሁፍ፡ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች ያለገደብ መፈቀድ አለባቸው፡፡ ይህም ዲሞክራሲያዊ ስርአት በትክክል ከስራ ላይ እንዲውል ከተፈለገ ወታደራዊው መንግስት በማያሻማ ቋንቋና በተግባር የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊ ትግል መደገፍ አለበት፤ ፀረሕዝብ ድርጊቶችን በሙሉ ማቆም አለበት፤ ተራማጅ የሰፊው ሕዝብ ወገኖችን ከአብዮታዊ ተግባራቸው ማደናቀፉ፡ ማሰሩ፡ ማንገላታቱ ቀርቶ መደገፍ ማበረታታት አለበት፡፡ ይህንን ካላደረገ ግን ውሎ ይደር እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሳይፋረዱት አይቀርም፡፡

የኢትዮጵያን አብዮት ከንግዲህ ወደሗላ የሚቀለብሰው ሃይል አይኖርም፡፡ ባገራችን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ይደረጋል፤ ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይደመሰሳሉ፡፡ ትግሉ ዉጣ—ዉረዱ የበዛበት ቢሆንም፤ ሌሊት አልፎ ቀን መተካቱ እንደማይቀር ሁሉ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ያሸንፋል!

ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንታገል!

<u>አጫጭር ዜናዎች</u>፡—

1. የአለም ባንክ የሚባለው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሳሪያ የሆነው ድርጅት፡ የአሜሪካን 'ኤይድ' እና ሌሎችም የምእራባውያን ባንኮችና የ'እርዳታ' ድርጅቶች በኢትዮጵያ ገጠር እርዳታ ካልስጠን ብለው ሰሞኑን ይመላለሳሉ፡፡ ለምን? የገጠሩን አብዮት ለመቀልበስ፡ የመሬት ንኡስ ከበርቴዎች እንዲፈጠሩና ገጠሩም የኢምፔሪያሊስቶች አሻንጉሊት በሆነ መንግስት ቁጥጥር ስር እንዲገባ ለማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ የአለም ባንክ የእህል ጅምላ ንግዱን የመንግስት ድርጅት እንዲይዘው ለማድረግ የሚያስችል ገንዘብ ለማበደር ራሱ ጠይቀአል፡፡ ሃሳቡ በተቻለ መጠን ከፍተኛ የመንግስት እህል ቦርድ ተቋቁሞ ለኢምፔሪያሊዝም ቁጥጥር የሚያመቹ ቢሮክራቶች እንዲያካሂዱትና በዚህ አማካይነት በገበሬ ማህበሮች ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ነው፡፡ የልማት ድርጅቶች በመንግስት ስር መሆናቸው የሚደገፍ ቢሆንም የሕዝብ ተሳትፎ ከሌለበትና መንግስቱ ራሱ ከሕዝብ ቁጥጥር ውጭ ከሆነ ግን አደገኛና የሚወገዝ ድርጊት ነው፡፡

2. ወታደራዊው መንግስት ስልጣኑን በኦፊሲየል እጁ ያገባበትን መስከረም 2 ቀን 'የአብዮት በአል' ብሎ ለማክበር ብዙ ዝግጅት በማድረግ ላይ ነው፤ ብዙ ገንዘብ በማውጣት ላይ ነው፡፡ የሚገርመውና የሚያሰዝነው ግን በዚሁ በአል ላይ እንዲካፈሉ የታዘዙት ከየገበሬው ማህበራት የሚላኩ አባላት ተፈሪ ሱሪና ጃኖ ጥለት ኩታ ለብሰው ይምጡ መባሉ ነው፡፡ የየራሳቸው አኩሪ ባህል ያላቸው ሕዝቦች፡ የስራ ልብሳቸው ወይም የራሳቸው የወግ ልብስ ቀርቶ የግድ ባለጃኖዎች ይሁኑ ማለት የቀድሞው መንግስት ያደርግ እንደነበረው የልዩ ልዩ ብሄሮችን ባህል ንቆ የሌላውን በላያቸው ላይ ከመጫን ሌላ ምንድነው?

3. ከጉልተኞችና በጠቅላላው ከአድሃሪያን ጋር ሕዝቡ ሰፊ የመደብ ትግል በሚያደርግበት በአሁኑ ወቅት የነደ/ አሸቱ ጨሌና የሌሎችም ተራማጆች ያለፍርድ በእስር ቤት መበስበስ በያንዳንዱ ተራማጅ አንጎል ውስጥ የሚጉላላ ጥያቄ ነው፡፡ አሁንም ደርጉ የመሬትን አዋጅ በትክክል በስራ ላይ ለማዋልና ሶሻሊዝምን ለማስፋፋት የሚጥሩትን ተራማጆች ማንገላታቱን ቀጥሎአል፡፡ የወላሞ አውራጃ አስተዳዳሪና የአውራጃው የመሬት ይዞታ ሰራተኛ በአድሃሪ የደርግ አባሎች አመጽ ታስረዋል፡፡ ከስራ አስኪያጆች ማሰልጠኛ የታሰሩት ሰራተኞች ያለፍርድ በከፊል ከርቸሌ ወርደዋል፡፡ ከጭላሉ እርሻ ልማት ድርጅትም እንዲሁ በርከት ያሉ ተራማጆች ታስረው ነበር፡፡ ተራማጅ የመሬት ይዞታ ሰራተኞች፡ ተራማጅ አስተዳዳሪዎችና ዘማቾች ወታደራዊው መንግስት ስለማይደግፋቸውና እንዲያውም ስለሚያስፈራራቸው የአድሃሪያንና የፖሊሶች ኢላማ ሆነዋል፡፡

4. ከሰኔ 27 እስከ 29 በጎንደር ከተማ የተደረገው የኢት.መምህራን ማህበር ጉባኤ ካሳለፋቸው አብዮታዊ ውሳኔዎች ጋር አያይዞ በክፍለአገሬ የደረሰውን ያስተዳደር በደል በሚገባ ገልጾአል፤ በክፍለአገሩ አስተዳዳሪ አማካይነት አድሃሪያን በሹመቱም በሽፍትነቱም እያሉ በበጌምድር በመመሸግ ላይ መሆናቸውንና አሁኑኑ ጥብቅ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚያስፈልግ አሳስቦአል፡፡